# ፅናት

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን






ቅጽ 1 ቁጥር 4 ቅዳሜ መጋቢት 18 ቀን 2002 ዓ.ም ዋጋ 2 ብር


# መድረክ አራተኛ ስብሰባውን አካሄደ

«ምርጫችሁ በእጃችሁ ነው::» — መድረክ

«እንመርጣችሂለን በርቱ» — ህዝቡ







## የመድረክ አመራርና ሕዝቡ በውይይት ላይ አስተያየት ሰጭ

የስምንት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብና ዋነኛ ተፎካካሪ የሆነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ አራተኛ ህዝባዊ ስብሰባውን በውሃ ልማት ሀብት ሚ/ር ከሁለት ሺ አምስት መቶ በለይ ሕዝብ በተገኘበት ውይይት አካሄደ::

ስብሰባው የወረዳ 17 የመድረክ ዕጩ ኢ/ር ግዛቸው፣አቶ አስራት ጣሴ የወረዳ 16 የመድረክ ዕጩ ተወዳዳሪ፣አቶ ንጉሴ ነውጤ የወረዳ 15 የመድረክ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲሁም የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የወረዳ 18 ዕጩ ተወዳዳሪ ያዘጋጁት ሲሆን እሁድ መጋቢት 12 ቀን 2002 ዓ.ም ከጧቱ 3:00 ሰዓት ጀምሮ ተካሂዷል::

በዕለቱ የመድረክ አመራሮች ወደ አዳራሹ ሲገቡ ህዝቡ ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ ችሯቸዋል:: ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው የመክፈቻ ንግግር ያሰሙ ሲሆን በአጠቃላይ አትዮጵያ በኢህአዴግ አገዛዝ የተጫነባትን ሁኔታ ዳሰዋል:: « አሁንም » አሉ ኢንጅነሩ « አሁንም ሚሊየነር ሆነ የሚባለው አርሶ አደር ጫማና የውስጥ ልብስ የሚባል አያውቅም:: ቤት የለውም ... ታዲያ ይሄን ማን ይለውጠው? » ሲሉ


(ወደ ገጽ ...6 ዞራል)


## ከውስጥ ገጾቻችን


- መብታችን ተገድቦ .. ገጽ 3
- ወጣት ወዲያ ... ገጽ 5
- ሕወሓት የትግራይን . . .ገጽ 6
- ኢህአዴግና ተቃዋሚዎች ... ገጽ 7


## በጅማ ዞን በመድረክ እጩ አባል ላይ የግድያ ሙከራ ተደረገ

በጅማ ዞን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) እጩ የክልል ም/ቤት ተወዳዳሪና የአንድነት ፓርቲ አባል በሆኑት በአቶ ታሪኩ መኮንን ላይ አራት ቦታ በጩቤ በመውጋት የግድያ ሙከራ መደረጉን የምዕራብና ምስራቅ ቀጣና ማስተባበሪያ ኃላፊ አቶ አስናቀ ሽንገማ ለፅናት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ገለፁ::

ከጅማ ዩኒቨርስቲ የዚህ አመት ተመራቂና የዩኒቨርስቲው ሰራተኛ የሆኑት አቶ ታሪኩ በ20/06/2002 ዓ.ም ከሌሊቱ 7:00 ሰዓት ላይ መኖርያ ቤታቸው ድረስ በመሄድ ጥቃት ፈፃሚዎቹ እንደሚያውቁት በመምሰልና ስሙን በመጥራት «ታሪኩ ድረስልን . . . አስጥለን» በማለት ሲጮሁ በር ከፍቶ ሲወጣ አራት ቦታ በጩቤ በመውጋት የሞተ መስሏቸው ጥለውት ሄደዋል:: በወቅቱ ቤተሰቦቹ ባደረጉት የድረሱልኝ ጩኸት ከጥቃት ፈፃሚዎቹ አንዱ ተይዞ ፖሊስ ባደረገው ማጣራት ከሊሙ ገነት ከተማ እንደመጣ ተናግሯል:: አቶ ታሪኩ በማህበራዊ ሕይወቱ ውስጥ ምንም ፀብ የሌለውና ተግባቢ ሲሆን ጥቃት ፈፃሚዎቹን ከዚህ በፊት አይቷቸው እንደማያውቅና ምናልባትም ተልዕኮ ሊኖራቸው እንደሚችል ተናግሯል ሲሉ አቶ አስናቀ ሽንገማ የምዕራብ ምስራቅ ቀጣና ማስተባበሪያ ኃላፊ ለፅናት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አስታውቀዋል::

# ምርጫችን በጃችን!!

# መልዕክተ ፅናት

## እውነት የማይዋጥለት ኢህአዴግ

የ2002 ምርጫ ቅስቀሳ አካል የሆነው በፓርቲ ዎች መካከል የሚደረገው ክርክር በተሌቪዥን እየታየ ነው:: በሬዲዮም እየተሰማ ነው:: የዚህ ዓይነት ውይይት በ1997 የተካሄደው በቀጥታ በተላለፈ ስርጭት ነበር:: በቀጥታ በመተላለፉ የሕዝብ አመኔታ ነበረበት:: በዚህ ሂደት ተቃዋሚዎች ፣በተለይም ቅንጅት ተ ጠቃሚ ነበር::

ኢህአዴግ ያቺ በ97 የታየችው የዴሞክራሲ ብልጭታ ለተቃዋሚዎች የሰጠችው ጠቀሜታ አስቆጭቶት በ2002 ያ ሁኔታ እንዳይደገም በሩን ዘጋ:: የዘንድሮው ክርክር ፤ ክርክር ከተ ባለ በቅድሚያ ተቀረጸ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ካዩት በኋላ የሚደረገው ተደርጐ እንዲተላለፍ ይደርጋል:: ኢህአዴግ በዚህ ክርክር ራሱ የውድድር አርእስት መራጭ ፣ራሱ እያንዳንዱ ተናጋሪ ሃሳቡን ለመግለጽ የሚወሰደውን ጊዜ ወሳኝ ራሱ ሳንሱር አድራጊ፣ ራሱ ተከራካሪ፣ ራሱ ዳኛ ሆኖ ቀርቧል:: በምርጫ ክርክር የመገናኛ ብዙሐንን አጠቃቀምን በተመለከተ አገራችን ወደ ፊት መሄድ ሲገባት በእጅጉ ወደኋላ ተንሸራታለች::

ክርክሩ በቀጥታ ለሕዝብ አይቀርብም ሲባል ወዲያው ስጋት አድሮብን ነበር:: ስጋቱም

የቀረቡ ሃሳቦች ሳንሱር ይደርጋሉ፤ ኢህአዴግ ሊሰማቸው የማይፈልግ ጉዳዮች፣ የማይዋጡለት እውነታዎች ይታፈናሉ የሚል ነበር:: የፈራነው አልቀረም ብዙም ሳይኬድ እውን መሆን ጀመረ:: መጋቢት 3 እና 4 2002 ዓ.ም የቀረበው ክርክር ዓርብ ጧት ሲቀርጽ መድረክን ወክለው የተከራከሩት አቶ አንዱዓለም አራጌ በርካታ እውነታዎችን አንስተ ው ተከራክረው እንደነበር አስታውሰው ነገር ግን ከእነዚህ እውነታዎች በርካታዎቹ ሳንሱር እንደተደረጉ ገልጸውልናል:: ሳንሱር ከተደረጉት እውነታዎች ሁለቱን እንደ ምሳሌ እንጥቅስ:: አንደኛው እውነታ የመሪያችን የወ/ት ብርቱካን መታሰርና ሰብአዊ መብት መጣስ የሕገመንግሥትና የአዋጅ አንቀጾች ተጠቅሰው የተረጋገጡበት ጉዳይ ነው:: ገዥው ፓርቲ የዚህ ጉዳይ እውነታ አልዋጥ ብሎት ሃሳቡን አፍኖ አስቀርቶታል:: ሁለተኛው እውነታ የዜጐች በሽመል መደበደብና በጅራፍ መገርፍ ነው:: በክርክሩ የቀረበው እውነታ በ21ኛ ው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ዜጐች ፣ ሴቶች ሳይቀሩ በሽመል ይደበደባሉ፣ በጅራፍ ይገረፋሉ የሚል ነው:: ይህ ደግሞ በስም በድምፅና በምስል ተቀርጾ በማንም ሊደመጥና ሊታይ የሚችል እውነታ ነው:: ይህም ታፍኗል:: የመግደል፣ የመገረፍና የመታሰር ጉዳይ በስቱዲዮ ቢቆርጡት፣ በየዕለቱ በገሃድ የሚታይ እውነታ ነው::

ኢህአዴግ እንደሰጐን ራሱን አሸዋ ውሰጥ ቀብሮ እንዳያይ ፣ ሕዝብም እንዲያውቅ ለማድረግ ያለውን እውነታዎች ለመታፈናቸው የተሰጠው ምክንያት የምርጫ ሥነ ምግባር ደንቡን ይፃረራሉ የሚል ነው:: እውነተኛ ሥነ ምግባር እውነትን አይደብቅም:: እውነትን የሚደብቅ እውነትን የሚፈራ ነው:: እውነትን ለመቀበል ድፍረቱ የሌ ላቸው ናቸው:: እውነትን የሚደብቁ የሃቀኝነት ባህሪ የሌላቸው ናቸው::

ኢህአዴግ በቀጥታና በግልጽ እንዲሁም በሀቀኝነት ከሕዝብ ጋር በሚደረግ ክርክር ሊያገኝ ያልቻለውን ጥንካሬ በምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ስም የሌሎችን ሃሳብ ሳንሱር በማድረግና በማዳከም ለማግኘት እየሞከረ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ዓይነት አካሄድ ንቀት እንጂ አክብሮት የለውም:: በዚህ ዓይነት አካሄድ ሽንፈት እንጂ ድል አይገኝም::

በግልጽ ውይይት ጥንካሬ ቢያጣ

ኢህአዴግ ገባበት በስቱዲዮ ቆረጣ

# መልዕክቶቻችሁ

*<u>ከሰሞኑ በሰልክና በጽሁፍ ከደረሱን ማልዕክቶች መሀከል ጥቂቶቹ:-</u>*

⇒ **ሀሎ ፅናቶች ! የመድረክም ሆነ የአንድነት ከፍተኛ አመራር አባላት በጥንቃቄ እንዲጓዙ ይችን መልዕክት አስተላልፉልኝ:: ገዥው ፓርቲ እምነት የሚጣልበት አይደለም:: ከሀዲ ነው:: ተናግሮ ያናግራችሁና በኋላ ለፍ/ቤት በማስረጃነት ያቀርባችኋል:: ለማንኛውም በርቱ ተበራቱ በልሉኝ::**

♦ *ለምክረዎእናመሰግናለን::መልዕክቱምበዚህ ይደርሳቸዋል::*

⇒ **ሀሎ ፅናቶች ! እናንተ ሰላማዊ ትግል እያላችሁ በየአጋጣሚው ትሰብካላችሁ::ለመሆኑ ኢሕአዴግን በካርድ ብታሸንፉት ሥልጣኑን እናንተ እንደምትመኙት በሰላም ይለቃል ብላችሁ ታስባላችሁ ? አሸፈረኝ ቢል እናንተ የምትወስዱት ርምጃ ምን ዓይነት ነው?**

♦ *በመጀመሪያ ደረጃ በካርድ እናሸንፈው:: ሥልጣን በሰላም አላሥ ረክብም ካለ ውሳኔው የሕዝብ ነው::*

⇒ **ሀሎ ፅናቶች! ወጣቶቻችሁን በመኪና ላይ ሆነው ቅስቀሳ ሲያደርጉ አይቻቸው አስቀንተውኛል:: ድፍረታቸው ወኔቸው ማረኮኛል:: እኔም ወጣት ነኝና አባል ለመሆን ቆርጬ ተነስቻለሁ ለመሆኑ መስፈርታችሁ ምንድን ነው?**

♦ *የመጀመሪያ መሥፈርታችን ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻ ነው:: ከዚያ ደግሞ ቆራጥ የሕዝብ ልጅ በመሆን የሕሊና ዝግጅት ማድ ረግ ነው:: ለማንኛውም ቢሮአችን ካሳንቺስ ባንቢስ የገቢያ ማዕ ከል ፊት ለፊት ስለሆነ ብቅ በልና እንነጋገር::*

## የዚህ ትውልድ ድርሻ ምን መሆን አለበት?

ከኢዮብ ሣለሞት

ከሕዝብ የተለየ ጥቅም ለማግኘት ከሸፍጠኞች ጋር መወዳጀት ነገ ያሳፍራል::ይህንን በተመለከተ አየን ራንድ የተባለ ሰዉ እንዲህ ይላል:-«ሌሎችን በማገልገል የሚኖር ሰው ባሪያ ነው:: የአካል ባርነት የሚያንገሸግሽ ከሆነ የመንፈስና የሕሊና ባርነት ፅንሰ ሐሳብ ደግሞ የቱን ያህል የበለጠ የሚያንገፈግፍ ነው:: በውጊያ ተሸንፎ ወደ አካላዊ ባርነት የተጋዙ ትንሽም ቢሆን የክብር አሸራ አላቸው:: ምክንያቱም አሻፈረኝ ብለው ታግለዋል፤ ሁኔታውን በመቃወም ተንፈራግጠዋል:: ነገር ግን ራሱን በፈቃደኝነት ለህሊና ባርነት የሰጠ ሰው ከፍጡራን ሁሉ የዘቀጠ ነው! » ብሏል::

እንደአለመታደል ሆኖ የአፍሪካ መሪዎች መከበር የሚሹት አዲስና ጠቃሚ ሃሳብ በማመንጨት ሳይሆን በጠመንጃ ነው:: ሀሳብ የማመንጨት ችሎታና ቀና መንፈስ ያላቸውን ሥልጣን ላይ ማን አድርሷቸው:: አሁን እያሳሰበኝ ያለው ግን የተተኪ ትውልድ በሀገር ጉዳይ ቸልተኛ መሆን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፅናት

በአንድነት ፓርቲ ኤዲቶሪያል ቦርድ የምትታተም በፖለቲካዊ፣ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩራ በ15 ቀን አንዴ የምትወጣ ጋዜጣ

<u>ዋና አዘጋጅ</u>

አንዳርጌ መሥፍን (አድራሻ :የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 የቤት ቁጥር (አዲስ)

ስ.ቁ 0913 05-69-42

ሪፖርተር: ዳንኤል ተፈራ

ስ.ቁ :-0911 035035

የኮምፒውተር ጽሑፍ:- ትግስት ቦጋለ

ሲ.ቁ 1910 142316

አታሚ

ሆራይዘን ማተሚያ ቤት

አድራሻ

ቂርቆስ ክ/ከተማ

ቀበሌ

17 የቤ.ቁ 124

<u>የአሳታሚው አድራሻ</u>

ቂርቆስ ክ/ከተማ

ቀበሌ 31 የቤት ቁጥር 461 ባምቢስ ሱፐር ማርኬት ፊት ለፊት



# ፖለቲካ

# መብታችን ተገድቦ ቤታችን አንቀመጥም!!

ከዝግጅት ክፍሉ

**«ነፃነታችንን አሜሪካ ወይንም ኦባማ እንዲሰጠን አንሻም! በኢህአዴግ ችሮታም እንዲሰጠን አንፈቅድም! ነፃነታችን በእጃችን ነው!!»**

*አቶ አበባየሁ ደሜ የአንድነት ፓርቲ የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ::*

**«መብታችን ተገድቦ ከቤታችን አንቀመጥም:: በትጥቅ ትግል ሣይሆን በምርጫ ካርድ ነፃነታችንን እንቀዳጃለን!!»**

*የተከበሩ አቶ ተመስገን ዘውዴ::*

**«የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሁልጊዜ መአት ወይም ብዙ ፊልም ይወስዳል፤ ግን ብልጭ የሚያደርገው ትንሽ ነገር እንኳን የለውም!»**

*ዶ/ር ኃይሉ አርአያ*

**«የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁሞ ይቅርታ መጠየቅ ክብር ነው!. . . እኔ እያልኩ ያሰሁት የሚበቃውን ክብር እንዲያገኝ እንታገል፤ነፃ እናውጣው . . . ስለፍቅር ነው መቆም ያለብን!!»**

*አቶ ስየ አብርሃ*

**«እስከ መገንጠል የሚለውን አላምንበትም ወደፊትም አላምንበትም!»**

*የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ*

ዕለቱ እሁድ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ነበር:: እሁድን በርካታ ኢትዮጵያውንና ኢትዮጵያውያት ከእረፍት በዘለለ በርካታ ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚሸፍኑበት መሆኑ ይታወቃል:: ከሥራ ቀኑ የበለጠ የተጣበበ ነው:: ልቅሶ መድረስ፣የታመመን መጠየቅ፣ዕድር፣ዕቁብ . . . የመሣሰሉትን ማሣካት የሚቻለው በዕለተ ሰንበት ነው:: እነዚህ ሁሉ ማኅበራዊ ችግሮች ሳይበግሯቸው ወይንም ከናካቴው ትተዋቸው መድረክ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ከኮተቤ፣ካቃቂ፣ከጉለሌ፣ከአዲስ ከተማ፣ከአራዳ ከየካ . . . በአጠቃላይ ከሩቅ ቦታ ወደ ወረዳ 20 ቂራ ቀበሌ 42 አዳራሽ ከ6 ሰዓት ጀምሮ ተመሙ:: አባላት፣ደጋፊዎች፣እንግዳ ደራሾች፣ወጣት ሴቶችና ወንዶች አረጋውያን በአዳራሹ ውስጥ ታደሙ::

ይህ የመድረኩ ስብሰባ ለሦስተኛ ጊዜ ሲሆን የመጀመሪያውን ስብሰባ ያካሄደው በጉለሌ ክፍለ ከተማ በድልበር አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ነበር:: ሁለተኛውን ያካሄደው ደግሞ በአዲስ ከተማ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አዳራሽ ሲሆን የመርካቶ ዙሪያና አካባቢዋ እንደመሆኑ መጠን አዳራሹ ጢቅ ብሎ ሞልቶ መቀመጫ ወንበር በመጥፋቱ ሕዝቡ ቁሞ ለመመልከት የተገደደበት ሁኔታ ነበር:: ኢትዮጵያዊ ጨዋነት፣ኢትዮጵያዊ ቁምነገር ምን ያህል እንደሚያኮራ ያረጋገጥንበት ያን ዕለት ነበር:: ሙቀቱም ሆነ መቆሙ ሳይሰለቻቸው በፅናት የስብሰባውን ፕሮግራም አጠናቀዋል::

የሦስተኛው የመድረክ ስብሰባም እንደ መርካቶ የተጨናነቀ ባይሆንም ወንበሮች በሙሉ ተይዘዋል:: የቆሙ ሰዎች ቢኖሩም በጣም ጥቂቶች ነበሩ::

ስብሰባውን በንግግር የከፈቱት የወቅቱ የመድረኩ ሊቀመንበር የተከበሩ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ሲሆኑ ንግግር ለማድረግ ሲቆሙ ታዳሚው በጭብጨባ ተቀብሏቸዋል::

ፕ/ር በየነ በንግግራቸው ወቅት ስለዴሞክራሲ እውን መሆን፣ስለኢኮኖሚ እንዲሁም ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ሲታገሉ የነበሩና በመታገል ላይ ያሉ በመሆናቸው ኩራት እንደሚሰማቸው አፅንኦት በመሥጠት ገልፀዋል:: ታዳሚውም አድናቆቱን በጭብጨባ ገልጸላቸዋል:: ፕ/ር በየነ ንግግራቸውን በመቀጠል የአዲስ አበባ ሕዝብ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጦች በተነሱ ቁጥር በግንባር ቀደምትነት እየተጋፈጠ ታላቅ መስዋዕትነትን እንደከፈለ ገልፀው ለአብነትም የ97 ዓ.ም የምርጫ ሂደት መጥቀስ በቂ ማረጋገጫ ነው ብለዋል:: «ዛሬ» አሉ ፕ/ር «ዛሬም ከተሳትፎ ወደ ድል የምንሸጋገርበት ወቅት ነውና መዘናጋት የለብንም:: በሀገር ጉዳይ ማኩረፍ፣ተስፋ መቁረጥ፣አይቻልምና የአዲስ አበባ ሕዝብ በተለመደው ትዕግስቱና አስተዋይነቱ ከጎናችን መቆም አለበት» በማለት ካስገነዘቡ በኋላ «በመሀከላችን የተከሰቱ ችግሮች ቢኖሩም በመወያየትና በመመካከር አስተካክለናቸዋል:: ወደ ፊትም ችግሮች ቢከሰቱም በምክክር እንፈታቸዋለን እንጂ አንከፋፈልም::» ሲሉ ቃል ገብተዋል:: በመጨረሻም «የሰላማዊ ትግል ግብ በምርጫ ማሸነፍ ነውና መድረክን ምርጡ!» በማለት የመክፈቻ ንግግራቸውን አጠናቀዋል::

ከፕ/ር በየነ ጴጥሮስ የመክፈቻ ንግግር ቀጥሎ ወደ ሌላ ጉዳይ ሳይገባ ከደረታቸው ላይ የብርቱካን ፎቶ ግራፍ የታተመበት ብጫ ካናቴራ የለበሱ ስድስት ወጣቶች በሰልፍ ወደ መድረኩ ሲወጡ የታዳሚው ሕዝብ አይኖች ከነሱ ላይ አተኮረ:: ወዲያው የሕዝብ ግንኙነቱ ጸሐፊ ወጣት መንግሥቱ ይስማ ወደ መድረኩ ፈጥኖ በመውጣት ስለወጣቶቹ ሳይሆን ስለለበሱት ብጫ ካናቴራ መግለፅ ሲጀምር ሕዝቡ ወደ ቆሙት ወጣቶች የበለጠ አነጣጠረ:: መንግሥቱ ይስማ እንዲህ አለ:- «እነዚህ ብጫ ካናቴራ ለብሰው ከፊታችሁ የቆሙ ወጣቶች ወ/ሪት ብርቱካን የታሰረችበትን አንደኛ ዓመት የቃሌ ምሽት አክብረው ሲመለሱ ከጎዳና ታፍሰው ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ያድራሉ:: ወንጀላቸው የብርቱካን ፎቶ ያለበትን ብጫ ካናቴራ «ብርቱካን ትፈታ» የሚለውን በጥቁር ቀለም የተፃፈበትን ለብሰው በመታየታቸው መሆኑን ጧት ይገለፅላቸውና ካናቴራውን ተነጥቀው ይባረራሉ:: ካንድ ወር ተኩል በኋላ ፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው ዳግመኛ «ብርቱካን ትፈታ» የሚል ካናቴራ እንዳይለብሱ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ «ብርቱካን ትፈታ» የሚለውንና «Free Birukan» በሚል በጥቁር ቀለም የተጻፈውን አጥፍተው ሰጧቸው ::ተመልከቱት!» ሲል የተደመሰሰውን ጽሑፍ ለሕዝቡ ካሣየ በኋላ «ሕዝብ አይቶ እንዲፈርድ፣የዴሞክራሲውን ጭንብል እንድታውቁት ነው ወደናንተ ያቀረብናቸው» በማለት ወጣቶቹን ይዞ መድረኩን ለቋል:: ሕዝቡ በመቆጨት ለትንሽ ጊዜ ሲያጉተመትም ይሰማ ነበር:: ወጣቶቹ የፖሊሶቹን ተግባር አጋልጠው መድረኩን ከለቀቁ በኋላ የመድረክ አስተዋዋቂዋ ወ/ሮ ላቀች ደገፉ መድረኩን በመረከብ በፕሮግራሙ መሠረት እጩዎች ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ጋበዙ:: በመጀመሪያ የደረሰው አቶ አበባየሁ ደሜ ነበር:: እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ:- «ነፃነታችንን አሜሪካ ወይንም ኦባማ እንዲሰጠን አንፈቅድም!ኢህአዴግም እንዲቸረን አንሻም ነፃነታችን በእጃችን ነው!!» በማለት ሲናገር የሞቀ ጭብጨባ ተችሮታል:: ከዚያም የሚወዳደርበትን ወረዳና የትምህርት ደረጃውንና እንዲሁም የሥራ ልምዱን ገልጾ ተቀመጠ::

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በበኩላቸው ወደ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች አትኩረው እየተመለከቱ «እናንተማ ፊልም ታነሳላችሁ:: ይሁን እንጂ ብልጭ የምታደርጓት ትንሽ ነገር እንኳን የላችሁም» በማለት የሰላ ሂስ ሰንዝረውባቸዋል:: የአዳራሹ ሕዝብም ንግግራቸውን በመደገፍ በጭብጨባ አጅቧቸዋል:: ዶ/ር ኃይሉ ንግግራቸውን በመቀጠል የቢ.ኤ. የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በአሜሪካን አገር እንዳገኙ ገልፀው ለረጅም ዓመታት በመምህርነት ማገልገላቸውን አውስተው ኢ.ሕአዴግ ከዩኒቨርስቲ ካባረራቸው 42 መምህራን መሀከል አንዱ እንደነበሩ ጠቅሰው ከሚወዱት ሙያ በመገለላቸውም ማዘናቸውን አልሸሸጉም:: ይሁን እንጂ ዶ/ር ኃይሉ አሁንም ሌላ ትልቅ ት/ቤት ውስጥ እንደገቡ በኩራት ገልፀዋል:: «ፓርቲ ት/ቤት ነው:: እማራለሁ፣ አስተምራለሁ» በማለት ሲናገሩ ሕዝቡ ፍቅርና አክብሮቱን በጭብጨባ ገልጾላቸዋል:: እንዲሁም አቶ አሥራት ጣሴ፣አቶ ኪዳኔ አርሶ፣አቶ ዓለሙ ጎቤቦ፣አቶ ባህታ ታደሰና ወ/ሮ ላቀች ደገፉ የሚወዳደሩባቸውን ወረዳዎች የትምህርት ደረጃቸውንና የሥራ ልምዳቸውን ለተሰብሳቢው ሕዝብ አስረድተዋል::

የእጩዎች ትውውቅ እንዳበቃ የመድረክ አስተዋዋቂዋ ወ/ሮ ላቀች ደገፉ ከተሰብሳቢዎች ጥቆማ ደረሰኝ ባሉት መሠረት አቶ ስየ አብርሃን በትግሉ ወቅት ኢ.ሕአዴግን መርተው አዲስ አበባ አድርሰውታል:: በሰላማዊ ትግሉስ አንድነትንና መድረክን የት ያደርሱታል? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ አቶ ስየ ሲመልሱ:-

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ

## ወጣት ወዴያ መንግሥት ወዲህ

**ከብሥራት ወ/ገብርኤል**

ወጣቱ ሥራን መስራት ቢፈልግም የሥራ ዕድሉ የጠበበ ብቻ ሳይሆን የማይታሰብም እየሆነ መጥቷል:: ምክንያቱ ግን ባለድርሻ አካል የሆነው ወጣቱ ቢያውቀውም መንግሥት በተለይም የሥራ አስፈፃሚ አካላት የገባቸው አይመስሉም::

ለአብነትም በአዲስ አበባ የሚገኙ የቀበሌ መዝናኛዎችና ተግባራቸውን ብንመለከት በተለይም ሳሪስ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቀበሌ 12/13 ጽ/ቤት ይገኛል:: በቀበሌው ጽ/ቤት ውስጥ የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ አለ:: ነገር ግን ተግባሩን በቅጡ እየተወጣ አይደለም::

የትኛውም ቀበሌ ጽ/ቤት የሚገኙ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ጉዳይ በአካባቢው ወይንም በቀበሌው የሚገኙ የወጣቶችን ደህንነት፣ጤና፣መዝናኛ የመሳሰሉ ይመለከታቸዋል፤ ግን አሁን በዓይን የሚታየወቻ አነስተኛ የፖለቲካ መጠቀሚያ ተቋምና የካድሬ ማሰልጠኛ እንዲሁም መዋያ ነው የሆኑት::

ሳሪስን ብንወስድ ከቀበሌው ጽ/ቤት ፊት ለፊት ተገትሮ የሺሻና የጫት ቤቶች ብዛት በእኔ እይታ ከአደስ አበባ በቀዳሚነት ደረጃ ይገኛል:: ልክ እንደ መርካቶ አእብዱ በረንዳ የጫት አዳራስ ባይኖርም ፊት ለፊት ሱቆች ጋር ተዳብለውና ተለጥፈው እንዲሁም መደብር ከፍተው ይሸጣሉ፤

ሺሻ ቤቶች ደግሞ ትንሽ ከዋናው አስፓልት ገባ ብሎ ይገኛል:: ታዲያ ይህ ብቻ አይደለም ሌሎችም ተግባራት ይከናወናሉ:: የሚገርመው ግን በአቅራቢያው ሁለት ትላልቅ አንድ የግልና አንድ የመንግሥት ከ1ኛ ደረጃ እስከመሰናዶ ያሉ ት/ቤቶችና ሌሎችመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ምን ይማራሉ?

አዳራሽ ሰርቶ ዲኤስ ቲቪ ቤት መክፈት ማለት ለወጣቶች መቆርቆርና መስራት ማለት ነውን? ይሄንናማ ወጣቱ እቤቱም ያገኘዋል:: ሊሆን የሚገባው ግን የአካባቢው ደህንነትና ጤንነት መጠበቅ ነበረበት እነኚህ ወጣቶች ፈልገውት ሳይሆን ሳይወዱ በግድ መጥፎ ነገርን እንደሚማሩ እና እንደሚለምዱ በነፍስ ወከፍ የሥነ-ባህሪ (የሳይኮሎጂ) ባለሙያ ያስፈልጋል? ያወይንስ እኛ የምንፈልገውን ካደረግን ስለትውልድ ምን ቸገረን በማለት?

ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ግን ከቀበሌው ጽ/ቤት ይልቅ የፌዴራል መንግሥት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያላቸው መስተጋብራዊ መዋቅር ነው:: ይህንንም በማስረጃ ላቅርብ:: ከመሰረቱ የነነበረው ችግር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ከወጣቶችና ስፖርት ሚኒስትር ጋር ተነጋግረው የሚሰሩ አይመስለኝም:: ለክ እንደመስሪያ ቤታቸው የቦታ ርቀት ልዩነትም አላቸው::ለምሳሌ የንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት የሚፈልገው ንግድ ተስፋፍቷል፣የሀገር ውስጥ ገቢንም አሳድገናል፣ለ2 እና 3 ሰው የስራ ዕድል ፈጥረናል:: ማለትን ብቻ ነው የሚያውቀው:: ግን የት ቦታ ምን ተሰራ? የትስ ቦታ ምን መሰራት አለበት? ታልሞም ይሆን ታስቦ የሚያውቅ አይመስለኝም:: ለወጣቱ የወደፊት ራዕይ ያለውን የሥራ አይነት የወጣቶችና የስፖርት ጉዳይ ቢሮ ደግሞ በግልፅ አይነግረንም::

በራሳቸው ጥረት እውቅና ያላቸውን አትሌቶች በፈረደበት አንድ ለአናቱ በሆነ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሲያሸንፍ እንዲታይና የፕሮግራም ማድመቂያ ያደርጋቸዋል:: ይህም ቢሆን ከእግዚአብሔር በታች በራሳቸው ጥረት የመጣ ነው::

ታዲያ ለወጣቶች መንግሥት የሰራውን ቢዘረዝርልን ብዙ «የኢህአዴግ ካድሬዎች አደራጅቻለሁ» ከማለት በስተቀር ይሄ ነው የሚባል ተጨባጭ ነገር አላየሁም:: ምክንያቱም ለወጣቱ ቢታሰብማ በሳሪስ ያለው ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ሺሻ ቤትና ጫት ቤት ባልተስፋፋ ነበ፤ በተጨማሪም የቀበሌው ጽ/ቤትም መከታተልና መቆጣጠር በቻለ ነበር፤ ግን ሲሆንም ሆነ ሲወራ አልታየም፤ አልተሰማም::

ይህን ሁሉ የደረደርኩት ለመግቢያ ያህል እንጂ በጥቅሉ ለማቅረብ አይደለም:: እውነታውን ትንሽ ላስቃኛችሁ::

ወጣቱ አመፀ፣ዘረፈ፣ሰረቀ፣አስገድዶ ደረፈ፣ረበሸ . . . ወዘተ ቢባል ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? የሚል አካል ግን አይሰማም:: ለዚህ ተግባር የሚዳርጋቸውን ምክንያት መንግሥት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እያበረታታ ነው::

ጫት የወጣቱን (የቋሚውን) የነርቭ ሥርዓት ከመደበኛው እጅግ በማስበለጥ ፈጣን ያደርገዋል፤የአስተሳሰብ ክህሎቱንም ከጤነኛ ሰው ባህሪ ለማላቀቅ እጅግ ፈጣን በማድረግ የማይችለውንና በእጁ ምንም ሳይጨብጥ ብዙ እንዳለው ያስባል፤የሥራ ባህሉን ተነሳሽነትን ይቀንሰዋል፤በምኞት ፈረስ ብቻ ይሰግራል፤ይጋለባል፤ሲነቃ ግን ራሱን ብቻ ያገኘዋል፤ያኔ ያለመውን ሲያጣና ለማግኘት ሲል ለአመፅ ይነሳሳል፤ ይዘርፋል፤ይሰርቃል፤ይረብሻል፤. . .ወዘተ የመሳሰሉትን ወንጀል በራሱም ሆነ በሌሎች ማህበረሰቦች ላይ ይፈፅማል::

ሌላው ደግሞ በጤናው ላይ በተለይም በተፈጥሮ ባህሪው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የሚገርምም፣የሚያስቅም፣የሚያሳዝንም ነው::

ጫት መቃም የሚያዘወትር ሰው የምላሱ ጣዕምን የሚለዩ የነርቭ ህዋሶች በፈሳሹ ኬሚካል ስለሚሸፈኑ የሚመገባቸው ነገሮች ሁሉ ጣፋጭና መራራ እንዲሁም ኮመጣጣና ጨዋማ መሆናቸውን መለየት ያስቸግረዋል:: በዚህም ከምግብ አብሳይ ከእናት ወይም ከእህት ጋር በጣፈጠ አልጣፈጠ ችግር ይጣላል ጠብም ሊፈጥር ይችላል:: (በሞኞች):: በተጨማሪም የምግብ ሥርዓት-ልማት ላይም ከፍተኛ ችግር ያስከትላል:: የኢኮኖሚውን ጉዳት ደግሞ ስናይ አንድ ቋሚ በትንሹ በቀን 20 ብር ቢያወጣ በወር 600 ( ስድስት መቶ) ብር ሲሆን በዓመት ሲሰላ ደግሞ 7200 (ሰባት ሺህ ሁለት መቶ) ብር ቢሆን ይህ ሰው ለአምስት ተከታታይ አመታት ቢቅም 36 000 (ሰላሳ ስድስት ሺህ) ብር ያባክናል ማለት ነው::

ታዲያ ይህ ወጣት በጤናው በስነ-ልቦና በማህበራዊ እና በኢኮናሚ እየተጐዳ መንግሥት የጫት ንግድን ሲያበረታታና ሲሸልም ይታያል:: እና የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ሴክተር ቢሮ ስራው ምንድነው? እስኪ ቆም ብላችሁ አስቡ! ወደዚህች ምድር ቀድሞ የመጣው ገንዘብ ነው ወይንስ ህይወት? መቅደም ያለበት የሰው ሕይወት ነው ወይንስ ገንዘብ?

ወጣቱ ገንዘብን በጤንነቱ ሰርቶ ማግኘት የሚቻል ሲሆን በገንዘብ ግን ወጣቱንም ሆነ ጉልበቱን ማግኘት አይቻልም:: ከዚያስ ይህችን አገርና ይህን ታላቅ ሕዝብ ማን ይተካ? ሳይባል ሱስ የተጠመደ መሪ እንኳን አገርንም ሲመራ በራሱ ዕውቀትና ችሎታ ሳይሆን በሚጠቀማቸው ሱሶች ይሆንና የሰው ችግር አይገባውም፤የራሱንም ችግር መፍታት አይችልም:: ለክ እንደ ጠንቋይ «ለራሱ አያውቅ ጠንቋይ ይለምናል ለነዳይ» እንዲሉ::

ሌላው የግለሰቡ ችግር እንዴት ከራስ አልፎ የአገር ችግር እንደሚሆን ስንመለከት መንግሥት አራት ሚሊዮን ዶላር በጫት የውጭ ሽያጭ ንግድ ገቢ ተገኘ ተብሎ ሽልማት ሲሰጥ እናንተም እንዴት? ልትሉኝ ትችላላችሁ በጥቂቱ እንደ አንድ ንፁህ ያልተበከለ ዜጋ ያሰላሁትን ቀመር ልንገራችሁ::

በአሁኑ ሰዓት በአማካይ በትንሹ ከአገራችን ሕዝቦች አራት በመቶ ጫት ቃሚ አለ እንበል:: ይህም በግምት ከ3 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ማለት ነው:: ይህ 3 ሚሊዮን ሕዝብ በትንሹ በቀን የ6 ብር ጫት ቢቅም በከንቱ በአንድ ቀን ውስጥ 18 ሚሊዮን ብር የአገሪቱ ወይም የሕዝቡ ሃብት ባክኗል:: እስኪ አስቡት ይህን በወር ስንቀይረው አምስት መቶ አርባ ሚሊዮን (540 ሚሊዮን) ብር ባክኗል::

ይህን 540 ሚሊዮን ብር ወደ አንድ ዓመት ሰንቀይረው 6 ቢሊዮን 480 ሚሊዮን (6.4 ሚሊዮን ብር) ገደማ የሕዝብ ሃብት ሲባክን ወደ አሜሪካን ዶላር ስንቀይረው ደግሞ አንዱን የአሜሪካን ዶላር በ13 ብር ምንዛሪ አስበን ስንቀይረው ከ498 ሚሊዮን ዶላር በላይ አገራችን በትንሹ ከስራለች እና ከ4 ሚሊዮን ዶላርና ከ498 ሚሊዮን ዶላር በቁጥርም ሆነ በዋጋ የቱ ይበልጣል? ይህንንም ከወጪ ቀሪ የሒሳብ ስሌት እይታ ብንመለከተው ከ498- 4 ሚሊዮን ዶላር እኩል ይሆናል:: 494 ሚሊዮን ዶላር በዜሮ አጥተናል::

በጥቅሉ በሰው ጤና ላይም ጉዳት አምጥቶ በአገሪቱ የሕዝብ ኢኮኖሚም ላይ ትልቅ ኪሳራ አስከትሎ የጫት ንግድ ሲበረታታ እና የወጣ ከምንም ሳይቆጠር ከግምትም ሳይገባ የአገር ኢኮኖሚ ከየትና እንዴት ወጣ? ኢኮኖሚዋስ አድጓል የተባለችው የትኛው ፕላኔት (ዓለም) ላይ ያለችው ኢትዮጵያ ነች?

መቼም በትንሹ ይህን ስሌት ያየ የእኛም ኢትዮጵያ የሚል ካለ ተሳስቷል ፈጹም ከእውነት የራቀ ነው ይህም ወጣቱን በአገሩ ጉዳይ ላይ በቀጥታ ባለድርሻና ተሳታፊ ባለመሆኑ ብቻ ነው ባይ ነኝ::




መድረክን በመምረጥ ነፃነትዎን ያረጋግጡ!!

# ካስተዋልነው

# ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ ከሌሎቹ ወገኖቹ ለመለየት የወረዱ አባባሎችን ተጠቅሟል

ከዝግጅት ክፍሉ

መድረክ ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 5 ቀን 2002 ዓ.ም በትግራይ ክልል ርእሰ ከተማ በመቀሌ ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሂዷል:: በስብሰባው ላይ የተገኙት የመድረክ ከፍተኛ አመራር አባላት

1. የወቀቱ የመድረክ ሊቀመንበር ኘ/ር በየነ ጴጥሮስ
2. ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
3. ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው
4. አቶ ስየ አብርሃ
5. አቶ ገብሩ አሥራት
6. ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
7. አቶ ቡልቻ ደመቅሳ
8. ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ
9. አቶ ሀዲ መሐመድ እና ሌሎቹም የተገኙ ሲሆን ሁሉም ተራ በተራ በትግርኛና በአማርኛ ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር አድርገዋል:: የመቀሌ ሕዝብ ከመሐል አገር ከሄዱ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ጋር ተሰብስቦ በተረጋጋ መንፈስ ሲወያይ ይህ ከ18 ዓመታት ወዲህ የመጀመሪያው በመሆኑ ትንግርት ያሰኘና ደስታን የፈነጠቀ ነበር:: አዳራሹ ጢም ብሎ ሞልቶ የተጨናነቀ እንደ ነበር ለማረጋገጥ ተችሏል:: የተሰብሳቢው ሕዝብ ብዛት በኢቲቪ ከአንድ ሺ በላይ እንደሆነ ቢገመትም በቦታው ላይ የነበሩ እንዳረጋገጡት ግን ወደ 4 ሺህ እንደሚጠጋ ይናገራሉ:: በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ የገኙው ፓረቲ ካድሬዎች አይረቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የስብሰባውን አቅጣጫ ለማደፍረስ ቢሞክሩም ሣይሳካላቸው ቀርቷል:: በመጨረሻም እንደማይሳካላቸው ሲያውቁ አዳራሹን ለቀው ወጥተዋል::

ተሰብሳቢው ሕዝብ የመድረክ አመራር ወደ አዳራሽ ሲገቡ በኢትዮጵያዊ ጨዋነት በሞቀ ጭብጨባ ተቀብሏቸዋል:: ከዚያም ውይይት ከመጀመሩ በፊት በቅርቡ በጩቤ ተወግተው ለተገደሉት የ2002 የመድረክ እጩ ተወዳዳሪ ለነበሩት ለአቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ የሕሊና ፀሎት ተደርጓል:: ከዚህ በኃላ የወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር ኘ/ር በየነ ጴጥሮስ የመግቢያ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም ወቅት ከዚህ በፊት የተለያዩ አቅጣጫዎችን ይዘው በተበታተነ መልኩ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ፓርቲዎች ተበታትኖ መታገሉ ርባነ ቢስ መሆኑን ተረድተው ካለፈው ዓመት ጀምረው 8 ፓርቲዎች ባንድ ላይ እየታገሉ ይገኛሉ ብለዋል:: በማጠቃለያ ንግግራቸውም መድረክ ጠንካራ አማራጭ መሆኑን ጠቅሰው መድረክን ምረጡ! ብለዋል::

ኢ/ር ግዛቸው በበኩላቸው የተሰብሳቢውን ሕዝብ ስሜት በሚነካ መልኩ ባደረጉት ንግግር ገዥው ፓርቲ በ97 ዓ.ም በቅንጅት ላይ ከሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲባል ብቻ እጅግ ኃላፊነት በጐደለው ሁኔታ ለትውልድ ጠንክረን በመትከል በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ መርዛማ ቅስቀሳ አካሂዷል ሲሉ በምሬት ገልፀዋል:: ኢ/ር ግዛቸው ንግግራቸውን በመቀጠል የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች የትግራይን ሕዝብ ከሌሎቹ ወገኖቹ ለመለየት ሲባል ወረዳና አልባሌ አባባሎችን በመጠቀም « ዕቃ ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ» በማለት ለማቆራረጥ ብዙ ጥረት እንዳደረጉ ጠቅሰው « ኢንተር ሃሞይ» የሚለውን የርዋንዳን የዘር ጭፍጭፍ በመጥቀስ ዋና የቅስቀሳና የመከራከሪያ አጀንዳቸው አድርገው እንደተጠቀሙበት አውስተው በዚህ ሁሉ ምክንያት የትግራይ ሕዝብ ስሜቱ ተጐድቷል» ካሉ በኃላ «እኛ አልንም አላልንም በተፈጠረው ክፍተት የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ እንጠይቃለን» ሲሉ ሕዝቡ እጅግ በሞቀ ጭብጨባ ድጋፉን ሰጥቷቸዋል:: ከኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ንግግር ቀጥሎ አቶ ስየ አብርሃ፣ አቶ ገብሩ አሥራትና ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ በትግርኛ ንግግር ያደረጉ ሲሆን የሶስቱም ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ የሁሉንም ለማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም:: የአቶ ስየ ንግግር የሁሉንም ጠቅልሎ የያዘ በመሆኑ የሳቸውን አለፍ አለፍ እያልን ለመቃኘት እንሞክራለን::

አቶ ስየ አብረሃ በመግቢያ ንግግራቸው ላይ « ከበርካታ ዓመታት በኃላ ከፊታችሁ ቁሜ ለመናገር በመብቃቴ የተሰማኝን ጥልቅ ደስታ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ» ካሉ በኃላ « ዛሬ እንኳን በሰላም አገናኘን በማለት የተጠቀምኩበትን ይህን አጋጣሚ የፈጠረልኝን መድረክ በሚባል የሚታወቀው ድርጅት ነው» ሲሉ መድረክንም አመስግነዋል:: በንግግራቸው ወቅትም ከመሰሎቻቸው ጋር በወጣትነት እድሜቸው ወደ በረሃ የገቡት የደርግን የአፈናና ፋሽሽታዊ አገዛዝ በማወስገድ በምትኩ ፍትህና ነፃነት የሰፈኑባት ሀገር ለመመሥረት እንደነበር አወስተው በመጨረሻ ግን የተመኙት ሁሉ እንዳልተሳካላቸው ጠቅሰው « ....ይህንን ኃላፊነት ወደ ጐን በተመተው ባንድ በኩል በትንቅንቁ ወቅት በተሰውት በስማቸው እየዘመሩና እየማሉ ራሰን የትግሉ ቢቸኛ ባለመብተና ፈጣሪ አድርጐ በማቅረብ በሕወሓት ባለሥልጣኖች የሚደረገው የታሪክ ስርቆት አሽቅድድሞሽ የሰላ ወቀሳ ሰንዝረዋል::

አቶ ስየ ከትግሉ አላማዎች አንዱና ዋናው ሥልጣንን መያዝ መሆን እንደነበር ገልፀው ነገር ግን በዚች አገር ላይ ዜጐች ያለ ሥጋት በመሉ ነፃነት ተገቢውን ክብርና ሰብአዊ መብታቸው እንዲጠበቅ ነበር አንዱ አላማቸው:: እነዚህ ሁሉ በተግባር ሣይወሉ በመቅረታቸው አንዱ የልዩነታቸው መንሰኤ እንደነበር አስረድተዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉድለቶችን እየተመለከተ በተለመደው ታጋሽነት የርምት ርምጃ እንድንወስድ ብዙ ጠብቆ ሳይሆን ቀርቷል:: ይህ ሁሉ ተደማምሮና ሰፍቶ በ 1991 ዓ.ም ሻቢያ ድንገት ወረራ በመክፈቱ ምክንያት ልዩነታቸው ይፋ መውጣቱን ተናግረዋል:: ይሁን እንጂ በነሐሴ ወር 1993 ዓ.ም ልዩነቶቻቸውን ለመፍታት ታስቦ ማ/ኮ ስብሰባ ተቀምጦ እንደነበርና የልዩነታቸው መንሥኤ ሉዓላዊነትና የአገር ጉዳይ ሆኖ ሳለ በውይይቱ ሂደት የሙስናና የዴሞክራሲ አጀንዳ አቅርበው ዋናውን ጉዳይ ለማስቀየር ተሞክሮ እንደነበር አመልክተው እንዲህ ይላሉ:-

« ..... የልዩነታችን መንሰኤ ሙሰና ከሆነ የሁላችንም ንብረት የፈተሸ» በማለት ሀሳብ አቅርበው እንደነበር ገልፀው ሙስና ብለው ለማደናገሪያነት ያቀረቡትን ሐሣብም ሳይገፉበት እንደቀሩ በቁጭት ይናገራሉ:: በመጨረሻ እንዳንዶቻቸው ከመንግሥት ኃላፊነታቸው እንደተነሱና ሌሎችም ከመላው ቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ ወህኒ መውረዳቸውን በምሬት ገልፀዋል:: ይህም አልበቃቸው ብሎ ታሳሪዎቹ ራሳቸውን ከማይከላከሉበት ወህኒ ቤት ሆነው እያሉ ሥማቸውን ጥላሸት ለመቀባት ጥረት መድረጉን በትዝብት ይናገራሉ:: «ይህም ሆኖ» ይላሉ አቶ ሰየ «ይህም ሆኖ ውሸትና ስንቅ እያደር ይቀላል እንዲሉ ያሁሉ የሙስና ወሬና አሉቧልታ እንደ ጉም ተበትኖ ደብዛው ጠፍቶ ቀርቷል» ብለዋል::

አቶ ሰየ ንግግራቸውን በመቀጠል « ሕወሐት ባንድ በኩል ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ መሆኑንና በዚያም እንደሚመራ ይገልፅና በሌላ በኩል ደግሞ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እንደሚከተልና በዚያም እንደሚመራ ይገልፃል:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ ደግሞ በባህሪው የመድብለ ፓርቲን ፅንሰ ሐሳብ አይቀበልም:: አብዮታዊ ዴሞክራሲያ ሁሉን ነገር በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርግ ነው:: ይህ መርህ በህገ መንግሥቱ ከሰፈሩ መርሆዎች ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው» በማለት ይተቻሉ:: አያይዘውም « የሕወሓት ሊቀመንበር በዘንድሮው የየካቲት 11 ቀን በዓል ላይ ያቀረበው ንግግርም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው» ብለዋል::

በመጨረሻም አቶ ሰየ የሕወሓት መሪዎችን ሲመክሩ « ... የሕወሓት መሪዎችን የማቀብላቸው መልዕክት አንድና ግልፅ ነው:: የናንተንማ ፍርድ ከዛሬ 18 ዓመት ጀምረን እናውቀዋለን:: ታስረን ፣ ተገርፈን ፣በፅናት ተቋቁመን ከዚህ ደርሰናል:: አሁን ደግሞ አበተራችሁ ሕዝቡ ፍርዱን እንዲሰጣችሁ ሁኔታዎችን መቻቹለት እንላችኋለን:: ባንድ እጅ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሌለው እጃችሁ ሕገ መንግሥቱን ይዛችሁ አታምታቱ:: ነፃና ፍትሕዊ ምርጫ አካሂዱ» ብለዋቸዋል:



## የመቀሌዉ ሕዝባዊ ስብሰባ

አቶ ስየ አብርሃ የባህር በርን በተመለከተም ዝም ብለው አላለፉም:: ቁርጠኛ አቋማቸውን ገልፀዋል:: « የኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት የተፈጥሮና የታሪካዊ መብት አላት የሚሉትን ወገኖች እንደ ዘረኞች በመቁጠር የሻቢያ ሸሪኮች ናቸው በማለት ጥላሸት ይቀቧቸዋል» ብለዋል:: በማጠቃለያ ንግግራቸው የጠቀሱት የወ/ሪት ብርቱካን ሚዲቅሳን በግፍ መታሰር ነው::

እንዲህ አሉ«እኔ ነፃነቴን አግኝቼ ከፊታችሁ ቆሜ እንድናገር እድል የሰጠችኝ ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ እውነትንና የሕግ መርሆዎችን በመከተል ፍትሕ የበየነችልኝ ነፃነቷ ተገፎ ወህኒ ቤት ትገኛለች:: በፖለቲካ አቋሟ ምክንያት የተቆለፈባት በር ሊከፈትላት ይገባል!» በማለት ጥሪ አቅርበዋል::

# መድረክ አራተኛ ...

ከገጽ 1 የዞረ

ጠይቀዋል:: አክለውም « የትውልድ ዕዳ አለብን ያን ዕዳ ለመክፈል ዴሞክራሲ አስፈላጊ ነው »

ብለዋል:: ያን መበሳቆል የፈጠረው የዴሞክራሲ እጦት እንደሆነ ለተሰብሳቢው ተናግረዋል:: ኢንጂነር ግዛቸው አያይዘውም «በየት እንደመጣ የማይታወቀው አብዮታዊ ዴሞክራሲም ሆነ ያለፉት አገዛዞች የኢትዮጵያን ችግር አልፈቱም:: አሁንም የኢትዮጵያ ህዝብ ይራባል፣ይጠማል፣ ለወጣቱም ቢሆን ያለችው ጥቂት ስራ የምትሰጠው በኢትዮጵያዊነት ሳይሆን በኢህአዴግ አባልነት ነው» ሲሉ ጠቅሰው መድረክ ይሄንን ለመለወጥ እየሰራ እንዳለና ህዝቡ ድምፅ ለመድረክ እንዲሰጥ ኢንጀነር ግዛቸው ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል::

በመቀጠልም ለታዳሚው ፅሁፍ ያቀረቡት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሲሆኑ በተለይም የአዲስ አበባ ኗሪ የንጉሱንም ሆነ የደርግን አገዛዝ ለመገርሰስ ያደረገውን ትንቅንቅና የነፃ መውጣት ፍላጐት ዘርዝረው አቅርበዋል:: ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ ህዝቡ እወነተኛ ለውጥና የሚፈልገውን ዴሞክራሲ ያገኝ መስሎት ነፍስ አድን የመጣ መስሎት ዘንባባ ይዞ ተቀብሎት ነበር:: ነገር ግን ኢህአዴግ የህዝቡን

ወደ ገጽ 7 ዞራል

# ሰዎች ምን ይላሉ?

# ምርጫ 2002 ኢህአዴግና ተቃዋሚዎች

**ከአለምነህ ደሴ**

ምርጫና የኢህዴግ ተቃዋሚዎች በምን ይለኩ? ኢህአዴግ በምርጫ 97 የደረሰበት ሽንፈት ዳግም እንዳይደርስበት አምስት አመት ሙሉ በእልህ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል:: የአባላቱን ቁጥር ለማባዛት ዜጐችን በማስገደድና በጥቀማጥቅም በመደለል ብዙ ደክሟል:: ነገር ግን የተሳካላት አይመስልም:: ኢህአዴግ እየገዛ ያለው ሆድ እንጂ ሕሊናን አይደለም:: ሆድ ደግሞ ከእለት የማስመሰል ድጋፍ አያልፍም:: እምነት በፍላጐት እንጅ በማስገደድና በጥቅም አይገኝም:: ኢሕዴግ እለታዊ ፍጆታ ለመጠቀም ያወጣው እቅድ የሰው ልጅን እንደ ቁስ ሲጠቀምበት ማየት ምን ያህል በሰው ልጅ ሰብአዊ ክብር ላይ እየቀለደ መሆኑን ማስተዋል ተችሏል::

በገዛ ሀገሩ ሠርቶ የመኖር መብቱን በተፈጥሮና በህግ ያገኘው የማይገሰስ መብቱን መርገጥ የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ከማደረግም አልፎ የጥቂት ተጠቃሚዎች የምኞት መደላድል ሲያደርጋቸው መታየቱ ምን ያህል በሰብአዊ መብት እየተቀለደ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው:: አወጣሁት የሚለውን የሚፎክርበትን ሕገ መንግሥት የአንድ ነጠላ ወረቀት ያህል ዋጋ ሳይሰጠው ፈረንጅን ለማታለልና ለማስመሰል ይጠቀምበታል:: ይሁን እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምንም ጥቅም የሰጠው የለም:: ሊሰጠውም አይችልም የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም::

ዛሬ ምርጫ 2002 በተቃረበበት ወቅት ኢህአዴግ ሚዲያውን በብቸኝነት በመቆጣጠር እኔን አድምጡኝ በማለት አሰልችና አደናጋሪ የሆነውን ፕሮፖጋንዳ ህዝብን ፊት ፊት እስኪለው ድረስ ይሰብካል:: አማራጭ የሌለው ሕዝብ መሔጃ የሌለው ሕዝብ ያዳምጠው ይሆናል እንጂ በተለይም በትላልቅ ከተሞች አድማጩ ጆሮውን ከከለከለ አመታት ተቆጥረዋል:: በተለይም ከምርጫ 97 በኃላ የኢህአዴግ ኢዲሞክራሲን ማመን ውሃን በእጅ እንደመጨበጥ ነው በማለት እንዲያውም የገዥው ፓርቲ ዜና እወጃ በሚቀርብበት «እንዴት አመሻችሁ» የዜና መግቢያን እያሾፈበት « እንዴት ዋላችሁ ዲሽ የሌላችሁ » በማለት ከሚፌዝበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ታዲያ ይህን የሰማ ይህን ያየ ጤናማ አይምሮ ያለው ሠው ኢሕዴግ የሕዝብ ድጋፍ አለው ማለት ይቻላልን ?

እንደወነቱ ከሆነ በዚች ደሀ ሀገር 95 ፓርቲ እንደ እንቁላል የተፈለፈለባት በእውነት የዴሞክራሲ ማበብን ያመለክታልን?

ዛሬ ኢሕአዴግ በምርጫ ዝግጅት ከፍተኛ መራወጥ ላይ ባለበት ሁኔታ የተቃዋሚዎችን ጽ/ቤት በመዝጋት አስተባባሪዎችንና አደራጆችን በማስፈራራት ጨለማን ተገን በማድረግ በመደብደብ አንዳንዶችንም በገንዘብ በመደለል ዘርፈ ብዙ ወከባ እያካሄደባቸው ይገኛል:: ዓላማውም የተቃዋሚዎችን እጩዎች ከምርጫው እንዲያፈገፍጉና በብቸኝነት እሱ ተወዳዳሪ ፣ እሱ ታዛቢ፣ እሱ ወኪል በመሆን አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ነው:: ይህንን ዓይነቱን አሠራርና አሳፋሪ የኢሕአዴግ አካሄድ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በቅርቡ በደቡብ ጐንደር በመዘዋወር ባይኔ አይቼ በጆሬዬ ሰምቼ ፣ ሕዝቡም ባገዛዙ ላይ ያለውን የመረረ ጥላቻ ለማጤን ችያለሁ::

እኔ በተወልድኩበት አካባቢ ተወዳዳሪ እንደመሆኔ መጠን ሕዝብ ሰብስቤ የፓርቲዬን ዓላማና ፕሮግራም ማስተዋወቅ ቀርቶ ከሁለትና ከሶስት ሰዎች ጋር እንኳን መነጋገር አልቻልኩም:: ሰው በፍርሃት ተሸሚቋል:: ሞራሉን ጥሏል:: ወኔው ተሰልቧል:: ኢሕአዴግውያን ብቻቸውን ያለአንዳች ተቀናቃኝ ይፈነጫሉ:: የተቃዋሚዎችን አደረጆች ግን ድርሽ አያስደርጓቸውም:: የ2002 ምርጫ በምን መልኩ «ነፃ ፣ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ» ሊባል እንደሚችል አይገባኝም:: በበኩሌ ከአጃቢነት ያለፈ ሚና አይኖርም የሚል እምነት አለኝ:: ይህም ሆኖ ተቃዋሚዎች እስከ መጨረሻዋ ዕለት ድረስ ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ ተጠቅመው እኩይ ተግባሩን በማጋለጥ ርቃኑን ማስቀረት ይኖርባቸዋል:: የሰላማዊ ትግል አንዱ ስልት አፈናና ጭቆናን ማጋለጥ ነው:: የቅርብ ጊዜ እቅዳችን በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን መጨበጥ ሲሆን የሩቅ ጊዜ ግባችን ደግሞ ይህንን የአፈና አገዛዝ ከሥር መሠረቱ ነቅሎ በመጣል የሕዝብን የበላይነት ማረጋገጥ ነው:: ይህ እስካልሆነ ድረስ ባንድ ወቅት በምርጫ ግርግር ሕዝብን በማደናገር ብቻ የሚቋጭ አይደለም::

በመሠረቱ እንዲህ ዓይነቱን የመብት ገፈፋና ሰብአዊ መብት ረገጣ በተቃዋሚዎች አቤቱታ ብቻ የሚወገድ አይደለም:: ባለመብቱ ሕዝብም ለነፃነቱና ለሰብአዊ መብቱ መታገል አለበት:: እያንዳንዱ ግለሰብ በነፃነቱ አሻፈረኝ ማለት አለበት:: ሰላማዊ ትግል ሲባል እጅንና እግሮቹን አጣጥፎ ከቤት በመቀመጥ በጥቂቶች መስዋዕትነት ብቻ የሚገኝ አይደለም:: ባለመብቱ ሕዝብ ቀጥታ የሰላማዊ ትግሉ ዋና ተዋናይ እስካልሆነ ድረስ በሹክሹክታና በፍርሃት ኢሕአዴግን ከሥልጣን ማውረድ ቀርቶ መነቅነቅም እይቻልም:: እያንዳንዳችን ኢሕዴግን « መብቴን ነፃነቴን፣ ነፍገኸኛል» ልንለው ይገባል:: እንዲህ ስንለውም ከአመፅና ከጥላቻ በፀዳ መልኩ መሆን አለበት:: የአመፅና የጦርነት ውጤቱ የሰው ሕይወት ማስቀጠፍና የሀገርን ንብረት ማውደም ነው::

ሁል ጊዜ ባፈሙዝ ሥልጣንን የምንጨብጥ ከሆነ ይች ሀገር ከድህነት ማጥ ውስጥ መወጣት አትችልም:: ውርሣችንም ጥላቻና ቂም በቀልተኝነት ነው:: ስለዚህ የሕዝብን የሥልጣን የበላይነት ለማረጋገጥ የ2002 ምርጫ ወሳኝ ነው:: ኢሕአዴግ የፈለገውን ያህል ቢወራጭ የሕዝብን እንቢተኛነት ማስቀየር አይችልም:: ሕዝብ በካርዱ ሥልጣኑን በአጁ መጨበጥ አለበት:: አሥመሳይ ተቃዋሚዎችንም ለይቶ በማወቅ ድምፁን ከነፈጋቸው ዳግም አይቀልዱበትም:: እውነተኛዎቹ ተፎካካሪዎች ኢሕአዴግና መድረክ ብቻ ናቸው:: ሌሎቹ ኢሕአዴግን እንዲያጅቡት የፈጠራቸው ፍጡሮቹ ናቸው:: በምንም መመዘኛ ተቃዋሚዎች አይደሉም:: በሕዝብ የሰቆቃ ኑሮ የሚቀልዱ ናቸው:: ስለዚህ ዓላማ ያለው ሕዝብ በማንም በምንም አይንበረከክም:: አይታለልም:: ቀጣይ ምርጫ እንኳን ሰው አትክል የሚቀጠፍበት መሆን የለበትም:: ፍርሃት የዘላለም ባርነት ሥለሆነ ከፍርሐት ተላቀን ነፃነታችንን ማወጅ አለብን:: ይህንን ሁሉ አሳክተን ኢሕአዴግ የሕዝብ ውሳኔን አልቀበልም ካለና አጭበርብሬ በሥልጣን ላይ እቆያለሁ « ወሾችም ይጮሀሉ:: ግመሏም ጉዞዋን ቀጥላለች» የሚለን ከሆነ የጊዜ ጉዳይ እንጂ የሰላምን አርማ ያነገቡ በመጨረሻ ድል ማድረጋቸው አይቀርም:: እንደ ደርግ ከሥጣኑ ተገፍትሮ ይወድቃል:: ለማንኛውም ቀድመን ፍቅርንና ቀናነትን ለኢሕአዴግ በማሳየት ለችግራችን የጋራ መፍትሄ እንድንፈልግ አሳስባለሁ::

## መድረክ አራተኛ ...

ከገጽ 6 የዞረ

የዴሞክራሲ ፍላጐት ሊያሟላ እንዳልቻለ አብራርተዋል::ዶ/ር ነጋሶ ኢህአዴግ አንዳንድ ማራኪ የሚመስሉ ነገር ግን ተፈፃሚነት የሌለቸው አንቀፆችን ጠቅሰው ገዥውን ፓርቲ ተችተዋል:: ከዚያም ዶክተሩ አንድ ጥያቄ አነሱ « ታዲያ መፍትሔው ምንድን ነው?» ሲሉ ከጠየቁ በኃላ «ነፃነታችን በእጃችን ነው::» በማለት ንግግራቸውን ቋጭተዋል::

በመቀጠልም መድረክን በመወከል አዲስ አበባ ላይ የቀረቡ ዕጩዎች ራሳቸውን አስተዋውቀዋል:: ሴቶችን በመወከል ወ/ሪት ልህልና ጉግሳ« የሴቶች ድምፅ » በሚል አንድ ፅሁፍ አቅርባለች:: ቀጣዩ የጥያቄና መልስ ክንውን ተካሄዷል:: ከጥያቄዎቹም መካከል:-

- እንኳን ሀገር ራሳችሁን ማስተዳደር አትችሉም እየተባላችሁ ነው:: እውነት ሀገር መምራት አትችሉም እንዴ?
- የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች ጥምረት ነው ይባላል:: ታዲያ እንዴት ኘሮግራማችሁ ይጣጣማልና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች ቀርበው ከመድረክ የሚከተለው መልስ ተሰጥቷል:: «እንዴውም ማስተዳደር የማይችለው ማን እንደሆነ እንተያይ:: ህዝብ ፊት እንከራከር:: በርካታ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ማገልገል የሚፈልጉ ስላሉ እነዚህን ሁሉ ማሳተፍ ይቻላል ኢህአዴግ ካምኘ ውስጥም ገብተን በቅንነት እያገለገሉ ያሉትን እናሳተፋለን » የሚል መልስ ተሰጥቷል:: መድረክ ሲያሸንፍ የኢትዮጵያ ወጣትና ምውሁራን ሀገር እንዲመሩ ያደርጋልም ተብሏል::ኢ/ር ግዛቸው በበኩላቸው « መምራት አትችሉም ተላላኪ፣ የቀለም አብዮተኞች ይሉናል:: ብቻ የማይሉን የለም:: ለመሆኑ ተላላኪው ማነው? አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት የቀለም አብዮተኞች አሉ:: በማግስቱ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የቀለም አብዮተኞች አሉና ወደታች ወረደ::» ሲሉ ገልፀዋል::

የተከበሩ አቶ ተመስገን ዘውዴም በበኩላቸው «ኢትዮጵያ በሰዎች ሳይሆን በሲስተም የምትመራ ሀገር እንድትሆን ነው የምንፈልገው» ብለዋል:: አያይዘውም «የዕዝ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ብለው ህዝቡ ደቦ ሲፈልግ ብሎኬት ያመርታሉ» ሲለ ትችታቸውን በገዥው ፓርቲ ላይ ሰንዝረዋል:: ኢህአዴግ ነፃ የሚባል ነገር አይገባውም ብለዋል::

አቶ አንዱዓለም አራጌ በበኩላቸው በክርክሩ ወቅት የተቆረጠባቸውን ለህዝቡ አሳውቀዋል:: በመጨረሻም የመዝጊያ ንግግር አቶ ንጉሴ ነውጤ አድርገው ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት የተጀመረው ስብሰባ ከቀኑ 7:00 ሰዓት ላይ በሰላም ተጠናቋል::

